# ፍቺ በዲ.ሲ

ፍቺ ጋብቻ የሚቋረጥበት ህጋዊ መንገድ ነው። የፍቺ ሂደቱን የሚጀምረው የትዳር ጓደኛ፣ በፍርድ ቤት ወረቀቱን በመሙላት ማመልከቻ የሚያስገባው አካል ከሳሽ ሲሆን፤ ሌላው የትዳር አጋር ደግሞ ተከሳሽ ይሆናል። ፍቺ በክርክር ወይም ያለክርክር ሊፈፀም ይችላል።

## በዲ.ሲ ለፍቺ ማመልከት ማስገባት እችላለሁ?

በዲሲ ለመፋታት ብቁ ለመሆን ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለብዎት፡ የነዋሪነት ማረጋገጫ፣ የጋብቻ ማረጋገጫ እና የንብረት ማረጋገጫ ሊኖርዎት ይገባል።

የነዋሪነት መስፈርቱን ለማሟላት የፍቺ አቤቱታዎን ባስገቡበት ወቅት እርስዎ ወይም ባለቤትዎ ቢያንስ ላለፉት ስድስት ወራት የዲ.ሲ ነዋሪ የነበሩ መሆን ይኖርቦታል።

የጋብቻ ማረጋገጫ መስፈርቱን ለማሟላት ከሳሹ በፍርድ ቤት ፊት ቀርቦ ፍቺ ሊፈፀምበት የሚበቃ ትክክለኛ የሆነ ጋብቻ መኖሩን ማረጋገጥ አለባቸው። ከሳሹ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ዋናው፡ ማለትም ዋናውን ወይም የተረጋገጠውን ቅጂ ነገር ግን ፎቶ ኮፒ ያልሆነ ማምጣት ይኖርበታል። እርስዎ እና ባለቤትዎ የተጋቡት በዲ.ሲ ከሆነ በዲ.ሲ በሚገኘው የጋብቻ ቢሮ ውስጥ አንድ ቅጂ ማግኘት ይችላሉ። ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ 500 Indiana Avenue, NW፣ ክፍል JM-690። የተለመደ ህግ ጋብቻ ካላችሁ የጋብቻ የምስክር ወረቀት አይኖርም፤ ስለሆነም ተከሳሹ የጋብቻውን ትክክለኛነት የጓደኞቻቸውን እና የቤተሰቦቹን ምስክርነት ወይም በሰነዶች አማካይነት ጋብቻው በተለመደ ህግ ተመስርቶ ያለ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

የነዚህን መነሻ መስፈርቶች ለማሟላት እርስዎና የትዳር ጓደኛዎ ለተወሰነ ጊዜ ተለያይታችሁ እንደነበር ማረጋገጥ አለብዎት። በዲ.ሲ የፍቺ ፍርድ አሰጣጥ ምክንያት አልባ ነው፤ ይህ ማለት ለፍቺ ሁለት ምክንያቶች ብቻ ናቸው እንዲቀርቡ የሚጠበቁት።

1. ስድስት ወር የጋራ እና የፈቃደኝነት መለያየት፡ እርሶ እና የትዳር አጋርዎ ለፍቺ ከማመልከትዎ በፊት ቢያንስ ላለፉት 6 ወራት በጋራ ተስማምታችሁ እና በፈቃደኝነት ለመለያየት ወስናችሁ ተለያይችሁ ያለምንም የጋራ ኑሮ(የፆታዊ ግንኙነትን ጨምሮ) እየኖራችሁ ከነበረ፤
2. የአንድ ዓመት መለያየት፡ ለመለያየት ቢስማሙም ባይስማሙም ለፍቺ ከማመልከትዎ በፊት እርስዎ እና የትዳር ጓደኛዎ ቢያንስ ላለፈው አንድ ዓመት ያለ ምንም የጋራ ኑሮ (የፆታዊ ግንኙነትን ጨምሮ) እየኖራችሁ ከነበረ፤

እርስዎ እና የትዳር ጓደኛዎ በአንድ ቤት ወይም አፓርታማ ውስጥ ቢኖሩም ተለያይተው መኖር ይችላሉ። ሆኖም ግን፤ በ “neither bed nor board” የፍቺ አይነት ስር ሆናችሁ የተለያየ ህይወት እንየመራችሁ እንደነበር ለፍርድ ቤት ማረጋገጥ አለባችሁ።

## ህጋዊ መለያየት ማለት ምን ማለት ነው? በዲ.ሲ ፍቺ ለመፈፀም ህጋዊ መለያየት ያስፈልገኛል ማለት ነው?

ለፍቺ ለማመልከት ህጋዊ መለያየት የግድ ሊኖርዎ አይገባም። ሕጋዊ መለያየት ማለት በትክክል ፍቺ ሳያገኙ የትዳር ጓደኛን በፍርድ ቤት የልጅ አሳዳጊነት መብትን ለማስከበር፣ የልጅ ድጋፍ ድጎማን፣ የአልሞኒ ገንዘብ ለመጠየቅ እና በትዳር የተፈራ ንብረትን ለመካፈል የሚያስችል መንገድ ነው። ምንም እንኳን የትዳር ጓደኞች ተለያይተው ለየብቻ ቢኖሩም እንዲሁም እነዚህ ህጋዊ ጉዳዮች መፍትሄ ቢያገኙም፤ እርስ በርሳቸው እንደተጋቡ ይቆያሉ እንደገና ለማግባትም ነፃ አይደሉም።

## ተከሳሽ ወይም ከሳሽ መሆኔ ልዩነት ይፈጥራል?

በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች አይፈጥርም፤ በፍቺ ጉዳይ ውስጥ ዋናው ልዩነት ፍቺው ተቀናቃኝ የሌለው ከሆነ ነው፤ በዚህ ሂደት ከሳሹ ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ በግልፅ ችሎት ሁኔታውን ሲያስረዳ ተከሳሹ በፍርድ ቤት ውስጥ ላይገኝ ሁሉ ይችላል። ፍቺው ተቀናቃኝ ካለው እና ሁለቱም ወገኖች ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ሁለቱም ወገኖች የሚገኙበት ችሎት ይኖራል። በፍርድ ሂደቱ ላይ ከሳሽ ማስረጃውን መጀመሪያ ያቀርባል።

## ተቀናቃኝ ያለበት እና ያለተቀናቃኝ በሚፈፀም ፍቺ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ፍቺው ተቀናቃኝ የለውም የምንለው እርስዎ እና የትዳር ጓደኛዎ በፍቺው ስትስማሙ እና ሙሉ ለሙሉ የጋብቻ ንብረትዎን (ንብረት እና ዕዳዎችንም ጨምሮ)፣ የልጆችን አስተዳደግ እና የልጅ ድጋፍ እንዲሁም አንድ የትዳር ጓደኛ ለአንዳቸው የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት እና እንደሌለበት ጨምሮ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ ስትችሉ ነው። ፍቺው ተቀናቃኝ ያለበት የሚሆነው እርስዎ እና የትዳር ጓደኛዎ ምንም እንኳ በፍቺው ላይ ስምምነት ቢኖራችሁም

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በአንዳቸውላይ ካልተስማማችሁ እና በፍርድ ቤት ወሳኔ እንዲሰጥ የምትጠይቁ ከሆነ ነው። ይህንን ማንበብ ይፈልጉ ይሆናል የልጅ ድጋፍ በዲ.ሲ፣ አልሞኒ በዲ.ሲ እና የልጅ አሳዳጊነት መብት እና ጉብኝት በዲ.ሲ።

## አሁን ፍቺውን አድርጌ እና ሁሉንምነገር በኋላ ማስተካከል እችላለሁ?

ሁኔ ታውይወስነዋል። አንድ ግዜ ፍቺውከተፈፀመእና ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ፍርድ ቤት ተመልሰውዳኛውን ስለ ጋብቻ ውስጥ ንብረትምሆነ ስለ ቀድሞየትዳር አጋር ተቆራጭ(አልሞኒ)መጠየቅ አይችሉም፤ እነዚህን ጉዳዮች እንዲፈቱ የሚፈልጉ ከሆነ በፍቺውወቅት እንዲፈቱ ሊያደርጓቸውይገባል። ነገር ግን ወደ ፍርድ ቤት ተመልሰውበመሄድ ዳኛውን የልጆች አሳዳጊነት መብት ወይምየልጅ ድጋፍ ትዕዛዝ እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ። ዲሲ የአሳዳጊነት መብት ለማስከበር ወይምየልጅ ድጋፍ ጥያቄ ለማቅረብ ትክክለኛውቦታውመሆኑን ለማረጋገጥ፤ የልጅ አሳዳጊነት መብት እና ጉብኝት በዲ.ሲ እና የልጅ ድጋፍ በዲሲ ያንብቡ።

## የጋብቻ ንብረት ምንድን ነው?

የጋብቻ ንብረት በትዳር ወስጥ የተገኙ ንብረቶችን እና ዕዳዎችን ይጨምራል። ንብረቶች ቤቶችን እና ሌሎች የሪል እስቴቶችን፣ ገንዘብ (የባንክ ሂሳቦች)፣ የግል ንብረት (እንደ የቤት እቃዎች ወይም መኪናዎች) እና የጡረታ ዕቅድ ጥቅሞችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ዕዳዎች ብድሮችን፣ የክሬዲት ካርድ ዕዳዎችን እና ታክስን ሊያካትቱ ይችላሉ። በዲ.ሲ ወስጥ በንብረት ላይ ወይም በዕዳ መክፈያውላይ ያለውስም ምንም ለውጥ የለውም፤ ወይንምአንደኛውየትዳር አጋር ለንብረቱ ቢከፈል ምንም ችግር የለውም።

የተለየ ንብረት የሚባለውአንድ የትዳር አጋር ከጋብቻ በፊት ያፈራውንብረቱ እና በትዳር ወስጥ በነበረበት ወቅት በሙሉ ለይቶ የያዘውንብረት ሲኖረውነው። የተለየ ንብረት አንድ የትዳር አጋር ለብቻ የተሰጠውማንኛውንም አይነት ስጦታ ወይም ውርስ በትዳር ወስጥ ሆኖም ቢሆን የተቀበለውንብረትን ያካትታል።

## እኔና ባለቤቴ የትኛውንብረት የጋብቻ ንብረት እንደሆነ እና እንዳልሆነ እንዲሁምማን ምን እንደሚያገኝ በመወሰን ላይ የማንስማማ ከሆነስ?

ከሁለታችሁ አንዳሁ ይህንን ወሳኔ ፍርድ ቤቱ ወሳኔ እንዲሰጥበት ከጠየቃችሁ ዳኛውየትኛውንብረት የጋብቻ ንብረት እንደሆኑ እና እንዳልሆነ ይወስናል፤ እንዲሁም "ፍትሀዊ እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ" የጋብቻ ንብረቶችን ያከፋፍላል። ህጉ ዳኛውየጋብቻን ንብረት በሚከፋፍልበት ጊዜ "ሁሉንምአስፈላጊ የሆኑ ነገሮች" ከግምት ወስጥ እንዲያስገባ ሕጉ ይደነግጋል።

## ስሜን ለመቀየር የምፈልግ ከሆነስ?

የትኛውምወገን ወደ ቀድሞስሙእየተመለሰ እስከሆነ ድረስ እና ለተጭበረበረ አላማ(እንደ ከእዳ ነፃ ለመሆን) እስካልሆነ ድረስ የስምለውጥ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላል።

## ያለተቀናቃኝ የሚፈፀምየፍቺ ጉዳይን እንዴት መጀመር እችላለሁ?

ተቀናቃኝ የሌለበት ፍቺ በፍርድ ቤቱ ስርዓት ወስጥ ተቀናቃኝ ካለበት ፍቺ በተሻለ የፍጥነት ሂደት ወስጥ ያልፋል። እርስዎ እና የትዳር ጓደኛዎ ለዋና ፍቺ ማመልከት እና በተመሳሳይ ግዜ የስምምነት መግለጫምላሽ መስጠት ይችላሉ፤ እንዲሁምከሳሹ ለተከሳሽ የፍርድ ቤት መጥሪያ ማድረስ አይጠበቅበትም። ይመልከቱፍቺ በዲሲ:ን ያለተቀናቃኝ ፍቺን ።

## ተቀናቃኝ ያለውየፍቺ ጉዳይን እንዴት መጀመር እችላለሁ?

እርሶ ጉዳዩን ከጀመሩ ከሳሽ ነዎት ማለት ነው። ለዋና ፍቺ ማመልከቻ ማስገባት የግድ ይኖርቦታል። በተጨማሪም የፍርድ ቤት ማዘዣ፣ የወሳኝ ሁነቶች መመዝገቢያ ቅፅ እና የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማጣቀሻ ቅጽ መሙላት ይኖርብዎታል። አቤቱታውን በሚያስገቡበት ወቅት ለመጀመሪያውየፍርድ ቤት ችሎት ቀን እና ሰዓት ቀጠሮ ይይዛል። ይህ መረጃ ለርስዎ ይቀርባል እንዲሁምለርስዎ ባለቤት የግድ መድረስ ባለበት የፍርድ ቤት ማዘዣወረቀት ላይ ይካተታል። አቤቱታዎን ካስገቡበኋላ፤ በዝርዝር ተለይቶ በተቀመጠውህግ መሰረት ለትዳር አጋርዎ የፍርድ ቤት ማዘዣወረቀቶቹን ማድረስ አለብዎት።

ይመልከቱበዲ.ሲ ወስጥ የፍርድ ቤት ማዘዣወረቀቶችን ማድረስን የፍቺ እና የአሳዳጊነት መብት ጉዳዮች የፍርድ ቤት ወረቀቶች ለሌላኛውወገን እንዴት እንደሚያደርሱ ተጨማሪ መረጃ ያገኛሉ።

የትዳር አጋርዎ ጉዳዩን ካስጀመሩ እርስዎ ተከሳሽ ይሆናሉ ማለት ነው። የአቤቱታውን ቅጂ በህጋዊ መንገድ ከደረስዎ በኋላ መልስዎን በ 21 ቀን ውስጥ ማስገባት አለብዎ። መልስዎን ካስገቡ በኋላ፤ ለትዳር ጓደኛዎ አንድ ቅጂ ማድረስ የግድ ይኖርቦታል።

ጉዳዩ የተቀናቃኝ ቢሆንም እንኳ ያለ ችሎት ችግሮቹን ሊፈቱት ይችሉ ይሆናል። የቤተሰብ ፍርድ ቤቱ በ Multi-Door Dispute Resolution Division (202-879-1549) አማካይነት ነፃ የማግባባት አገልግሎት የሚሰጡ ከእርስዎ እና ከባለቤትዎ ጋር የፍቺ ፍላጎቶችዎን በማደራደር የሚሰሩ የሰለጠኑ ባለሞያዎችን ያቀርባል።

## የፍቺው የመጨረሻ ጊዜ መቼ ነው?

ዳኛው ፍቺዎን ሲያፀድቅ የፍቺውን ማዘዣ ቅጂ የፍርድ ችሎቱ እንዳበቃ ወዲያውኑ ያገኛሉ ወይም በፖስታ ይላክሎታል። ፍቺዎ የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ በፍርድ ቤቱ ማህተም ተደርጎበት “ወደ መዝገብ ቤት ከገባ” በኋላ ባሉት 30 ቀናት ይጠናቀቃል፤ ይህም ችሎቱ ከተጠናቀቀ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሊሆን ይችላል። ከሁለቱም ወገኖች በ 30 ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማስገባት እና ፍርድ ቤቱ የፍቺን ትእዛዝ እንዲያቆይ መጠየቅ ይቻላል። የይቆይ ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ፤ ይግባኙ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ትዕዛዙ የመጨረሻ ሳይሆን ይቆያል። የይቆይ ጥያቄው ውድቅ ከተደረገ፤ ይግባኙ እየተወሰነ እያለ ትእዛዙ በተግባር ላይ እንደዋለ ይቀጥላል። ሁለታችሁም የዳኛውን ትእዛዝ ይግባኝ ላለመጠየቅ ከተስማማቹ፣ የጋራ የይግባኝ ጥያቄ አለማንሳት በማስገባት 30 ቀን ሳትጠብቁ ወሳኔው ወዲያው ይጠናቀቃል።

አስፈላጊ የሆኑትን የፍርድ ቤት የፅሁፍ ክስ (ህጋዊ ሰነዶች) በ www.dcbar.org/pleadings ወይም ዲሲ ላይ ማግኘት ይችላሉ። ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከል ማዕከላዊ ማእከል ( ክፍል JM-540) ከሰኞ እስከ ዓርብ 8:30 a.m. to 5:00 p.m ድረስ ክፍት ነው።